# SY23-24 የ‘Duke Ellington’ የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት: የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ከ9-12 ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች

**ስለ ‘Duke Ellington’ የስነ-ጥበባት ትምህርት ቤት (Ellington) - የመግቢያ መስፈርቶች (Admissions Criteria)**: በ‘Ellington’ ውስጥ፣ ለስዕል የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ እና የስነጥበብ ዜጎችን የሚያበረታቱ፣ እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ አልፈው የሚሰሩ – ጥብቅ የሆነ የኮሌድ ቅድመዝግጅት የጊዜ ሰሌዳን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ፤ ቅድመ-ባለሙያዊ የሆነ የስዕል ስልጠናዎችን ለመውሰድ ትጋትን በማሳየት የሚሰሩ ምሁሮችን እንፈልጋለን። ምንም እንኳን የውጤት ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም እንኳን፤ በሁሉ የክፍል ስራዎቻቸው ላይ ጥረት የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ስለ ‘Ellington’ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ‘Ellington’ ውስጥ፣ ሁሉም አመልካቾቻችን፣ እንደ መጀመሪያ የማመልከቻቸው አካል አድርገው፤ ጽሁፍ (essay)፣ ሪፖርት ካርድ፣ እና ሦስት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) እንዲያስገቡ እንጠይቃለን። የ‘My School DC’ ሎተሪ ማመልከቻቸውን በሚገባ ያስገቡ ሁሉም የሎተሪ አመልካቾች፤ በማቅረቢያ (audition) ውስጥ ለመካፈል ብቁ ናቸው። ለመግቢያ፤ በአነስተኛነት ሊገኝ የሚገባ (minimum) የGPA የውጤት ደረጃ (Score) የለም።

‘Ellington’፣ ወደ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚገቡ አመልካቾች ላይ - ከስነጥበብ (arts) ትምህርት ቤት እስከተላለፉ ድረስ እና በቂ የሆነ የስነጥበባት ክሬዲቶች (arts credits)  እስካላቸው ድረስ እና ሊያጠኑት ካሰቡት ኮርሶቻቸው ጋር በተመሣሣይነት እስካላቸው ድረስ ምልከታ-እንደሚያደርግ፤ እባካችሁ አስተውሉ።

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። አመልካቶች፤ እንደ ግለሰቦች ሆነው የሚገመገሙ እና በትምህርት ቤቱ የስነጥበብ (arts) ፕሮግራሞች ከሚፈልጋቸው ጎን-ለጎን ሆኖ ይመዘናሉ። ከእያንዳንዱ የስነጥበብ (art) መምሪያ ውስጥ ከፍተኛ ውጤቶችን ያገኙ ተማሪዎች፣ ብቁ ሆነው ይለያዩ።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች፡** |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ምልከታ (GPA እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/Attendance) | 10% | ‘Ellington’ የውጤት-ደረጃዎች (GPA) ላይ ምልከታ የሚያደርግ እና እንደ የሪፖርት ካርድ አንዱ አካል በማድረግ የትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት የመረጃ-ስብስብ (attendance data)ን፣ ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) GPA ወይም አስፈላጊ የሆነ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) የለም፤ ነገር ግን ማመልከቻው፣ ለመግባት (admission) እንዲታይ ለማድረግ፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት። |

| | | |
|---|---|---|
| | | የ'D' ወይም የ'F' ውጤት ያገኙ ተማሪዎች፣ ወይም ከአምስት በላይ መቅረቶችን በሪፖርት ካርድ/በሂደት ሪፖርቱ ላይ ያስመዘገቡ፤ የበለጠ መረጃዎችን ወይም ዝርዝሮችን በቤተሰባቸው ቃለ-መጠይቅ ጊዜ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |
| ጽሁፍ (Essay): በ'My School DC' ማመልከቻ ውስጥ | 10% | በፕሮግራማችን ላይ የተማሪውን ፍላጎት ለማወቅ፣ ለማህበረሰቡ ያላውን ቁርጠኝነት፣ እና የግል ጽናት ተሞክሮን ለማንጸባረቅ፤ ጽሁፉ (essay) - በጥቅም-ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay)፣ በ'My School DC' ማመልከቻ አማካኝነት የሚጠናቀቅ ነው።<br><br>**ማስታወሻ፡** ተማሪው እንደሚያመለክትበት ክፍል/department መሠረት-አድርጎ፤ ተጨማሪ ጽሁፎችን (essays)፣ የጽሁፍ ናሙናዎች (writing samples)፣ ወይም ቁሳቁሶች (materials)ን - በ'My School DC' ማመልከቻ አማካኝነት ወይም በቀጥታ ወደ ተማሪው ወደሚያመለክትባቸው ክፍሎቹ (departments) በኢሜል አማካኝነት፣ እንዲያስገቡ የሚያስፈልጋቸው ሊሆን ይችላል። እነዚህ ተጨማሪ ቁሳቁሶች (materials)፣ እንደ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ ክፍል አንዱ አካል ሆኖ የሚገመገም ይሆናል።<br><br>ጽሁፎች (Essays)፤ በእያንዳንዱ የስነጥበብ መምሪያ እና የመግቢያ (Admissions) ቡድን ምልከታ የሚደረግበት ይሆናል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ የጽሁፎች (essays) ግምገማ ላይ ለብቻው ያተኮረ አይሆንም። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 10% | የ'Ellington'፣ የተማሪውን በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን-ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና በቀለም ትምህርት የሚያገኙት ውጤቶች ይዘትን ለመስጠት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>'Ellington'፣ ሦስት (3) የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን ይጠይቃል። አመልካቾች፤ አስተማሪዎቻቸው እነሱን-ወክለው ድጋፍ-መስጫውን (recommendation) እንዲያስገቡላቸው፣ የሚቻለውን ጥረት-ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ እና በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። |

| | | |
|---|---|---|
| | | በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪውን የኢሜል አድራሻዎች ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታል።<br><br>መደመጦቹ (auditions)፣ የማመልከቻ የማብቂያ ቀንን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚከናወን ሆኖ በመገኘቱ፣ ድጋፍ ሰጪዎች (recommenders)፣ የሚፈለገውን የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) በቂ በሆነ ጊዜ ማዘጋጀት እንዲችሉ፣ አመልካቾች ከማብቂያው ቀነ-ገደብ በሚገባ ቀደም ብሎ ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ እናበረታታለን። 'Ellington'፣ የአመልካቹን ትምህርት ቤት በቀጥታ-በመደወል፣ ተማሪውን በተመለከተ መረጃዎችን ለማግኘት መደወል ይችላል።<br><br>ድጋፍ-መስጫዎች (recommendations) በሆነ-ምክንያት ካልገቡ፤ ትምህርት ቤቱ፣ ስለ አስተዳደራዊ ችሎታዎች፣ የጊዜ-አጠቃቀም ችሎታ፣ በርካታ-ነገሮችን በአንድ-ላይ ስለመስራት እና ስለተማሪው ቅድሚያ-ሰጥቶ የመስራት ችሎታዎች ጥያቄዎችን ሊጠይቅ ይችላል። |

| | | |
|---|---|---|
| የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ | 50% | የ'My School DC' ማመልከቻቸውን፣ በሎተሪ ማውጫው ውስጥ በተሳካ-ሁኔታ ያስገቡ ሁሉም አመልካቾች፤ በማቅረቢያ (audition) ወይም ፖርትፎሊዮ (portfolio) ምልከታ ውስጥ ለመካፈል ብቁ ይሆናሉ። በተመረጡት መምሪያቸው መሠረት፣ ተማሪዎች ተጨማሪ ቁሳቁሶችን (materials)፤ ጉድ ፎተግራፍን ጨምሮ (ከዚህ በፊት በMy School DC' ማመልከቻ በኩል ካልገባ)፣ ፖርትፎሊዮ (portfolio)/የስራ ናሙና፣ ወዘተ... እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። እነዚህ ቁሳቁሶች (materials)፣ (እንደ የተፃፈ ናሙናዎች፣ ፖርትፎሊዮ፣ ወዘተ...)  ተማሪው ወደሚያመለክትበት ክፍሉ ዋና-መሪዎች (department heads) ወደሆኑ በቀጥታ በኢሜል አማካኝነት ምእግባት ያለበት እና እንደ በማቅረብ-መደመጥ (Audition)/ፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ አንዱ አካል በመሆን ይገመገማል። ለተጨማሪ መረጃ፣ Audition Procedures ን ይመልከቱ።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-መልኩ፤ ለSY23-24 መደመጦቹ (auditions)፣ እንደየአስፈላጊነቱ እና በሁኔታዎች-አመላካችነት ላይ መሠረት በማድረግ፣ በርቀት (virtually) የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችል-ይሆናል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል።<br><br>ዝርዝር የሆነ ትዕዛዞችን፣ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታን ለማጠናቀቅ እርዳታ ወይም ማመቻቻ (accommodation) ለሚያስፈልጓቸው ማንኛውም ተማሪዎች፣ መረጃን እና ቀጣይ |

| | | |
|---|---|---|
| | | እርምጃዎችን ጨምሮ፤ ለሁሉም ተማሪዎች ይላካል። በተጨማሪም፣ እርዳታ እና ማመቻቻዎች (Support and accommodations)፣ በዓመቱ ሙሉ በትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ ላይም ማግኘት ይቻላል። |
| **መደመጡን (audition) እና የማመልከቻውን ምልከታ አቀራረብን ያለፉ ተማሪዎች ብቻ፣ በሂደቱ ቀጣይ እርምጃዎችን በመቀጠል እንዲያከናውኑ ይጋበዛሉ።** | | |
| የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) | መሰተፍ ያስፈልጋል* | የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) አላማው፤ መደመጣቸውን (audition) ያለፉ ቤተሰቦችን እና ተማሪዎች፣ ከመምሪያ ጋር ተገናኝተው ለመምሪያው-ልዩ-ሆነው የሚጠበቁባቸውን ለመመልከት እና በዚያ ዙሪያ ስላለው ጥናት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ነው። |
| ቃለ-መጠይቅ | 10% | ‘Ellington’፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ፣ እና ጽናትን ማሳየት የሚችሉ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣትን አበክሮ ያምንበታል። ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (ለምሳሌ እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪውን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ እንጠይቃቸዋለን። በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-መልኩ፤ ለSY23-24 ቃለ-መጠይቆች፣ እንደየአስፈላጊነቱ እና በDCPS ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፤ ይየጤና መመሪያን ለመከተል እና ሁኔታዎችን እየተቆጣጠሩ ለመቆየት ባለው ቁርጠኝነት፤ ቃለ-መጠይቆቹ -በርቀት (virtually) የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችል-ይሆናል። |
| የመግቢያ ምልከታ (Admissions Review) | 10% | የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የመግቢያ (Admissions) ኮሚቴው (ርዕሰ መምህር፣ የውጪ ጉዳዮች ዳይሬክተር፣ ረዳት- ርዕሰ መምህራን፣ የተማሪዎች ዲን (Dean)፣ አስተማሪዎች እና/ወይም የመምሪያው መሪዎች) አጠቃላይ ማመልከቻውን የሚመለከቱ እና የመጨረሻ የብቁነት ውሳኔዎችን ለመስጠት የመጨረሻ አስተያየትን ይሰጣሉ። |

**የቀለም-ትምህርት ምደባ ግምገማ (Academic Placement Assessment):** በ'Ellington' ውስጥ፣ ለተማሪው ተገቢ-የሆነውን የክፍል-ምደባዎች ለማወቅ እንዲያስችለን እና ሌላ ማንኛውንም የሚያስፈልግ እርዳታዎችን ለመለየት እንድንችል፤ ሁሉንም አዲስ መጪ-ለሆኑ ተማሪዎች፤ የቀለም-ትምህርት ምደባ ግምገማ (Academic Placement Assessment)ን እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን። የቀለም-ትምህርት ምደባ ግምገማ (Academic Placement Assessment)፤ ከተማሪው ለመግባት (admission) የብቁነት ሁኔታ ጋር በተያያዘ የደረጃ-አሰጣጥ አይኖረውም። ብቁ-ናቸው ተብሎ የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ይህን ፈተና ይወስዳሉ፣ እና ፈተናውን መውሰድ እንደ መስፈርት-ሆኖ የሚያስፈልግ ነው። በአስቸኳይ-ድንገተኛ ሁኔታ ወይም በጊዜ-ሰሌዳ መጋጨት ምክንያት ይህን ፈተና በአካል-ተገኝቶ (in-person) መውሰድ ካልቻላችሁ፣ አማራጭ-የማስተካከያ እርምጃ ሊደረግ ይችላሉ። እባክዎን ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ። በተጨማሪም፣ በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-ሁኔታ፣ በSY23-24 ውስጥ፣ የቀለም-ትምህርት ምደባ ግምገማው (Academic Placement Assessment)፣ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችል-ይሆናል።